| | |
|---|---|
| ዐይነት ፤ | ዐምዳዊ ፡ ጽሑፍ ፤ "መሥራች ፡ ጽሑፍ ።" |
| ርእስ ፤ | "የኢትዮጵያ ፡ ሥልጣኔ ፦ ሥልጡንሕዝብና ። ኢትዮጵያና ፡ ሥርዐቷ ።" |
| ደራሲ ፤ | ነጋ ፡ ኀይለ ፡ ሥላሴ ። |
| ዕለት ፤ | ጥቅምት ፡ 1990 ፡ ዓ.ም. ። |
| ዝግጅት ፤ | ፍጹም ። |
| መጽሔት ፤ | "ሥልጡንሕዝብና" ፥ ቍ.2012-003 ። |
| ማስታወሻ ፤ | |
| ማሳሰቢያ ፤ | (ከ 22 ፡ ዓመት ፡ በኋላ ፥ ጥር ፡ 2012 ፡ ዓ.ም. ፡ ዳግመኛ ፡ የወጣ ። ) |

# መሥራች ፡ ጽሑፍ ።

founding article | article fondateur | مَقالة تاسيسي

# የኢትዮጵያ ፡ ሥልጣኔ ፦ ሥልጡንሕዝብና ። ኢትዮጵያና ፡ ሥርዐቷ ።

ነጋ ፡ ኀይለ ፡ ሥላሴ ።

(ሥልጡንሕዝብና ፥ 7ኛ ፡ ዓመት ፥ ቍ.009 ፥ ጥቅምት ፡ 1990 ፡ ዓ.ም. ። )

---

የኢትዮጵያ ፡ ሕዝብ ፡ ገዥ ፡ ነው ፤ ሕገ ፡ መንግሥቱን ፡ መሥራት ፡ የእግዚእናው ፡ የተቀደሰ ፡ መብቱም ፡ ተግባሩም ፡ ነው ።

ኢትዮጵያ ፤

ሀ. ፡ **በብሔርነት** [1] ፤ እኹለት ፡ የብሶች ፥ አፍሪቃና ፡ እስያ ፡ መገናኛ ፡ ላይ ፥ ባየርም ፣ በየብስም ፣ በባሕርም ፡ የማትለያይ ፤ ዙሪያዋን ፡ በምድረ ፡ በዳ ፡ ታጥራ ፥ በውሃ ፡ የተቀጠረችና ፥ በቃጥላ ፡ ታቅባ ፡ ለግሏ ፡ የበለጸገች ፡ የገነት ፡ ተራራ ፡ ነች ።

በ. ፡ **በሕዝብና** [2] ፤ ሦስቱን ፡ አንጋድ ፡ (ካምን ፥ ሴምን ፥ ያፌትን) ፡ በዐናት ፡ አዋሕዳ ፥ በሐረግ ፡ እያዛወገች ፥ በቦታ ፡ እያዋገነች ፡ አውርዳ ፥ ሰፊ ፡ ብሔሯን ፡ አልብሳ ፥ በሰው ፡ ዘርም ፡ በመሬትም ፡ በትውፊትም ፡ የማትከፋፈል ፡ አንዷት ፡ ልዩ ፡ ሀገር ፡ ኾናለች ።

ገ. ፡ **በዕድል** ፤ ከተፈጥሮ ፡ ያጣችው ፡ ብሔራዊም ፡ ኾነ ፡ ሰብአዊ ፥ ንዋያዊም ፡ ኾነ ፡ መንፈሳዊ ፡ ጸጋ ፡ ስለሌለ ፥ ወሰን ፡ ዐልፎ ፡ የሌላን ፡ አገር ፡ የመውረር ፡ ፍላጎት ፡ ልታነቃ ፥ ወይም ፡ ሌላን ፡ ሕዝብ ፡ የማጥቃት ፡ ክፋት ፡ ልታለማ ፡ ምክንያት ፡ የሌላት ፥ የማይኖራት ፡ ፍጹም ፡ ሰላማዊት ፡ ናት ። ይህም ፡ ሊታመን ፥ በሀገርነት ፡ ከተገኘችበት ፡ ጊዜ ፡ አንሥቶ ፡ እስካኹን ፡ ድረስ ፥ ሲያጠቋት ፡ ባልቀማም ፡ ባይ ፡ ታጋይ ፥ ባልሞት ፡ ባይ ፡ ተጋዳይነት ፡ ከመከላከል ፡ በቀር ፥ ጠብ ፡ አጭራ ፣ ጦር ፡ ወርውራ ፣ አገር ፡ ወራ ፡ የተዋጋችበት ፡ ድርስ ፡ የለም ፤ ኖሮም ፡ አያውቅ ። ይኸውም ፥ ከ፫ ፡ ሺሕ ፡ ዘመን ፡ ባላነሰ ፡ የዓለም ፡ ታሪክና ፡ የቅዱሳት ፡ መጻሕፍት ፡ ዜና ፡ የተመሰከረላት ፡ ነው ።

ደ. ፡ **ባገዛዝ ፡ ባህል** ፤ እያንዳንዱ ፡ ተወላጅ ፣ እያንዳንዱ ፡ ጐሣና ፡ እያንዳንዱ ፡ ነገድ ፡ እኩል ፡ የኢትዮጵያ ፡ ነው ፡ ባለበት ፡ መንገድ ፥ ኢትዮጵያም ፡ የያንዳንዱ ፡ ተወላጅ ፣ የያንዳንዱ ፡ ጐሣ ፣ የያንዳንዱ ፡ ነገድ ፡ ናት ፡ ሲል ፡ [የኢትዮጵያ ፡ ሕዝብ] ፡ ያምናል ። በዚህም ፡ የማይናወጽ ፡ እምነቱ ፡ ላይ ፤

- *«ሊያደርጉልኽ ፡ የምትወደውን ፥ አንተም ፡ ለመሰልኽ ፡ አድርግለት ። »* ፡ በሚያሠኘው ፡ አምላካዊ ፡ ትእዛዝ ፡ አመናዝላ ፡ ባለማቻት ፡ ርትዕ ፥ ኅብረተሰቧን ፡ ሠርታ ፤
- በቃል ፡ ኪዳን ፡ ያስተሳሰረችውን ፡ ዐልጋዋን ፡ ዘርግታ ፤
- ወዷ ፡ የመረጠችውን ፡ መስፍን ፡ "ሐፃኔ ፡ ሀገር" ፡ እያሠኘች ፤
- ቀጥሎም ፥ በኀላፊነት ፡ ሲለያዩ ፥ በሥልጣን ፡ ተመዛዝነው ፥ በሱታፌያቸው ፡ ህላዌያቸውን ፡ የሚያለሙ ፡ "ሐጋጊ" ፥ "ፈጻሚ" ፡ ኹለት ፡ ደንቦች ፡ የቃል ፡ ኪዳን ፡ መንግሥት ፡ አቁማ ፥ ንጉሥ ፡ እያነገሠች ፤

ከዚያም ፥ መደምደሚያውን ፥ ኹለት ፡ ዘርዐ ፡ ነገሥት ፡ ያዋሐደ ፣ ኹለት ፡ ሕዝብ ፡ ያዛመደ ፣ ዐሥራ ፡ ዐምስት ፡ ነገሥታት ፡ ላይ ፡ በኹለት ፡ ነገሥታት ፡ በመሠየሙ ፡ "ንጉሠ ፡ ነገሥት" ፡ በተሠኘ ፡ እግዚእዋ ፡ (ገዢዋ) ፡ ራሷን ፡ በራሷ ፡ ስትገዛ ፡ በሙሉ ፡ ሐርነት ፡ የኖረች ፥ በባህል ፡ የበሰለች ፥ በትውፊት ፡ የበለጸገች ፥ በነጻነት ፡ የከበረች ፥ ፍጹም ፡ እግዝእት ፥ ፍጹም ፡ ሰላማዊት ፥ ሥልጡንሕዝባዊት ፡ አገር ፡ ናት ።

ባላቸው ፡ የማይወሰኑ ፥ የሌላን ፡ የማያከብሩ ፥ ኹሉን ፡ ለራሴ ፥ ለራሴ ፡ ብቻ ፡ የሚሉ ፡ አገሮች ፥ ከጥንት ፡ አንሥተው ፡ ሲወጓት ፡ ኖረዋል ። በዚህ ፡ በምናገባድደው ፡ ምዓመት [3] ፡ እንኳ ፥ የተፈጥሮ ፡ ወሰኗን ፡ በግፍ ፡

---

1 **ብሔር** ፤ ምድር ። [አዘጋጅ]

2 **ሕዝብና** ፤ ሕዝብነት ። [አዘጋጅ]

3 **ምዓመት** ፤ ምእት ፡ ዓመት ፥ ወይም ፡ ምእትያ ። [አዘጋጅ]


©ኢ.ሀ.ሥ.አ. ፥ 2012 ፡ ዓ.ም. ።

እየጣሱ ፥ ልትቋቋመው ፡ በማትችለው ፡ ጦር ፡ ስድስት ፡ ጊዜ ፡ ያኽል ፡ ወሯዋታል ። ቅዱስ ፡ ዳዊት ፦ *«ኢትዮጵያ ፡ ታበጽሕ ፡ እደዊሃ ፡ ኀበ ፡ እግዚአብሔር»* ፡ ሲል ፥ አስቀድሞ ፡ እንደ ፡ ተነበየላት ፥ ሙሉ ፡ እምነቷን ፡ በርሱ ፡ ላይ ፡ እያደረገች ፡ ባትጋደልና ፥ ሲያምኑት ፡ የማይከዳው ፡ አምላኳ ፡ በቸርነቱ ፡ ባይታደጋት ፡ ኖሮ ፥ እስካኹን ፡ ሳያጠፏት ፡ ባልቀሩም ፡ ነበር ።

ብፁዕ ፡ አቡነ ፡ ተክለ ፡ ሃይማኖት ፥ በትንብልናቸው ፥ የኢትዮጵያን ፡ መንግሥት ፡ ከዐምባ ፡ ገነናዊው ፡ የዛጔ ፡ ዘር ፡ ወደ ፡ ሕጋዊው ፤ ትውፊታዊው ፤ ሰሎሞናዊው ፡ ዘርዐ ፡ ነገሥት ፡ ሲያዛውሩ ፥ የኢትዮጵያ ፡ ሕዝብ ፥ ዳር ፡ እስከ ፡ ዳር ፡ ወዶ ፡ ፈቅዶ ፡ በወከላቸው ፡ በዘጠና ፡ ዘጠኝ ፡ ክፍላተ ፡ ሀገር ፡ አፈ ፡ ጉባኤዎቹ ፡ ሰውነት ፥ በሀገራዊ ፡ አኳኋ ፡ ችሎት ፡ በዐማራ ፡ ሣይንት ፡ (ሠየምት) ፡ ተሰብስቦ ፥ ንግሥት ፡ ማክዳ ፥ ቀድሞ ፥ የቀዳማዊ ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ ዐፄ ፡ ምኒልክን ፡ መንግሥት ፡ አዝንታና ፡ አጽንታ ፡ ያቆመችበትን ፤ *«ሕዝብ ፡ አንጋሽ ፤ መስፍን ፡ ነጋሽ ፤ ቤተ ፡ እግዚአብሔር ፡ ቀዳሽ»* [4] ፡ ያሠኘውን ፡ የሥነ ፡ ግዛት ፡ ባህልና ፥ ከዚያም ፡ ወዲህ ፡ በየጊዜው ፡ እየደረሰ ፡ እያዩትም ፡ እየሠሩበትም ፡ የተገነዘቡትን ፡ ፍልስፍና ፡ ተጨማሪ ፡ በማድረግ ፥ በወግ ፡ መክረው ፡ ዘክረውና ፥ በሙሉ ፡ ድምፅ ፡ ወስነው ፥ በቋንቋው ፡ ቀዳሚነት ፤ ጥራትና ፡ በተናጋሪው ፡ ብዛት ፥ ነገሥተ ፡ ዛጔ ፥ ሀገራዊ ፡ የመንግሥት ፡ ዕውቅ ፡ ልሳን ፡ አድርገውት ፡ በኖረው ፡ ዐማርኛ ፥ ለመዠመሪያ ፡ ጊዜ ፥ የተጻፈ ፡ ዐፄ ፡ ሥር [5] ፡ ለመዠመሪያ ፡ ጊዜ ፡ ዐማራ ፡ ሣይንት ፡ ላይ ፡ በሀገራዊ ፡ ዕርቀ ፡ ሰላም ፥ ሚያዝያ ፡ ፩ ፡ ቀን ፥ ፲፱፻፳ ፡ ዓ. ፡ ም. ፡ ዐወጀ ።

የኢትዮጵያ ፡ ሕዝብ ፥ ከጥንት ፡ አንሥቶ ፥ በሰላምም ፡ ኾነ ፡ በጦርነት ፡ ጊዜ ፥ በሕገኛ ፡ እንደራሴዎቹ ፡ ችሎት ፡ ሀገራዊ ፡ እግዚእናውን ፡ እያገዘፈ ፥ መክሮ ፡ ዘክሮ ፡ በሚያለማት ፡ ርትዕ ፡ መንግሥቱን ፡ እየሠራና ፡ ንጉሡን ፡ እያነገሠ ፥ ራሱን ፡ በራሱ ፤ ለራሱ ፡ ሲገዛ ፡ የኖረ ፡ ሐራ ፡ ሕዝብ ፡ ነው ። ይኸውም ፡ በታሪክ ፡ የታወቀ ፡ እውን ፡ ስለ ፡ ኾነ ፥ አስረጅ ፡ ፍለጋ ፡ የሚያስኬድ ፡ ግዳጅ ፡ የለበትም ። በጦርነት ፡ ዘመን ፡ ለተባለው ፡ ምሳሌ ፡ መጥቀስ ፡ ቢያሻ ፡ ግን ፥ ዐፄ ፡ ድል ፡ ነዐድን ፤ ዐፄ ፡ ገላውዴዎስን ፥ ንግሥተ ፡ ነገሥታት ፡ ዘውዲቱንና ፡ መላከ ፡ ፀሐይ ፡ ኢያሱን ፡ ማመልከት ፡ ይቻላል ።

ሕገ ፡ መንግሥት ፡ መሥራት ፤ ንጉሥ ፡ ማንገሥና ፡ በራስ ፡ ማደር ፡ ከቶ ፡ ለኢትዮጵያ ፡ ሕዝብ ፡ ዐዲሱ ፡ አይዶሉም ። ዐብሮ ፡ በቀሉ ፤ ባሕርያዊ ፡ ችሎቱ ፥ ለማንም ፡ ማን ፡ የማይለቀው ፡ የእግዚእና ፡ ጕልማዊ ፡ መብቱም ፡ ኀላፊነቱም ፡ ነው ። የራሱ ፡ ጌታ ፡ ስለ ፡ ኾነ ፥ ራሱን ፡ የሚያሳድርበትን ፡ ሕጉን ፡ የሚወስነውና ፡ ድርጅቱን ፡ የሚሠራው ፡ ራሱ ፤ ባለቤቱ ፡ ነው ፡ እንጂ ፡ ሌላ ፡ አይዶለም ፥ አይኾንም ። ራሱ ፡ ሳለም ፥ ሌላ ፡ ማንም ፡ ልሥራልኽ ፡ ሊለው ፡ መብት ፡ የለው ። ፈቃዱን ፡ ተራምዶ ፥ ልሥራ ፡ ብሎ ፡ ቢነሣ ፡ ግን ፥ እግዚእናውን ፡ ገፎ ፡ ባሪያው ፡ ሊያደርገው ፥ ወይም ፥ ካኹን ፡ በፊት ፥ አነስ ፡ ተለቅ ፡ ያሉ ፡ ሦስት ፡ አራት ፡ ወራሪዎች ፡ ሕዝቦች ፡ ሞክረውት ፡ እንደ ፡ ነበረው ፡ ኹሉ ፥ ርሱን ፡ ከምድረ ፡ ገጽ ፡ አጥፍቶ ፥ በተፈጥሮ ፡ አቀማመጧ ፡ ያራቱን ፡ የብሶች ፡ የምድር ፤ ያየርና ፡ የባሕር ፡ መገናኛዎችን ፡ የምትቈጣጠር ፥ ያፍሪቃ ፡ ቀርን ፤ የሰሜን ፡ ምሥራቅ ፡ አፍሪቃን ፡ አገሮች ፡ ጕረሮ ፡ የምትመግቢቱን ፡ አገሩን ፥ ኢትዮጵያን ፡ ለመውረስና ፡ አፍሪቃን ፡ ለመግዛት ፥ ዐረብን ፡ ለማጥላትና ፡ የዓለምን ፡ ዛኅን ፡ ለመገልበጥ ፡ ሊኾን ፡ የማያጠራጥር ፡ ነው ። እንቢ ፡ ሊለው ፡ ይገባዋል ። ይኸውም ፥ ሀገራዊ ፡ ባህሉ ፤ ሕግጋቱ ፡ ኹሉ ፡ የሚያውቁለት ፡ መብቱ ፡ ነው ። ልሥራልኽ ፡ ብሎ ፡ በኀይል ፡ ቢነሣ ፡ ግን ፥ አሻፈረኝ ፡ ብሎ ፡ ሊከላከለው ፡ ይገደዳል ፤ ያልቀማም ፡ ባይ ፡ ታጋይ ፤ ያልሞት ፡ ባይ ፡ ተጋዳይነት ፡ ተግባሩ ፥ የተቀደሰ ፡ ብሔራዊ ፡ መብቱ ፤ ሰብኣዊ ፡ ክብሩ ፡ ነው ። ይህኑም ፡ የዓለም ፡ መንግሥታት ፡ ሕግ ፡ አስተካክሎ ፡ ያውቅለታል ፤ ርሱም ፡ ሥራውን ፡ ያውቅበታል ፨

4 በክርስትና ፡ *«ሕዝብ ፡ አንጋሽ ፤ መስፍን ፡ ነጋሽ ፤ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ቀዳሽ»* ፡ ተብሏል ። [አዘጋጅ]

5 <u>**ዐፄ ፡ ሥር**</u> ፤ ሕገ ፡ መንግሥት ፡ ወይም ፡ ክዋኔ ። [አዘጋጅ]


©ኢ.ሀ.ሥ.አ. ፥ 2012 ፡ ዓ.ም. ።